# በስደት ከኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አባላት አስተባባሪ ኮሚቴ

## Coordinating Committee of Exiled members of Ethiopian Teachers Association

የተሰጠ መግለጫ

ሚያዚያ 18, 2004

**የመምህራን ትግል በማስፈራራትና በውሸት ውንጀላ አይኮላሽም !!**

በአሁኑ ወቅት የተከሰተው የመምህራን እምቢ ባይነት እንዲያው እንደ ደራሽ ጎርፍ ድንገተኛ ክስተት ሆኖ ያለፈ ወይም የሚያልፍ አይደለም። በሃያ ዓመታት የወያኔ/ኢህአዴግ የግፍ አገዛዝ ሲያካሂዱት የቆየ የትግል አካል ነው። የትግሉን ስልት ለየት ያደረገው ነገር አለ ቢባል ግን በወቅቱ ያነሱት የዳቦ ጥያቄ በህልውና ላይ የተንጠለጠለ መሆኑ ላይ ነው። ወደኋላ መለስ ብለን ብናስታውስ በአገሪቱ ሕገመንግሥትና በዓለም አቀፍ ድንጋጌዎች መሠረት በነፃ መደራጀትና በሙያ ማህበራቸው ዙሪያ መሰብሰብ እንዲችሉ በመታገል ውጣ ውረዱ አስከፊ ሆኖባቸዋል። ወያኔ ከህግ በላይ ሆኖ አለም አቀፉንም ሆነ ራሱ አስከብረዋለሁ የሚለውን የራሱን ሕገመንግሥት ጥሶ በመምህራንና በማህበራቸው ላይ ጥቃት አውጇል።

ወያኔ/ኢህአዴግ በመምህራንና በማህበራቸው ላይ ያደረሰውን የውንብድና  እርምጃ ደጋግመን ከማንሳት ተቆጥበን ትኩስ ትኩሱን እኩይ ተግባር ላማሳየት እንገደዳለን።የ አካል፤የ አእምሮ፤የ ሞራል፤ የፍትሕ...ድቀት በተሞላ ጉዞ መምህራን ፍርሃት፤ሥጋት እንግልትና ወከባ ቀስፎ ይዟቸው እየቆዘሙ ቆዩ። በአገሪቱ የሚታየው የኑሮ ውድነት ሲታከልበት በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ ሆኖ ነገሮች ሁሉ ከሚችሉት በላይ ጣራ ነኩ። ይህ በእንዲህ እንዳለ ነው የወያኔ ት/ሚ/ር በተገኘበት ድሬዳዋ ላይ በተደረገዉ የትምህርት እመራር ስብሰባ ላይ  ተለጣፊ መምህራን ማህበር ተብዬ ስለደመወዝ እርከን ማስተካከያ /ጭማሪ ጥያቄ የተነሳው።ጥያቄው በዚህ አካል ይቀርባል ተብሎ የሚጠበቅ ባይሆንም ዕውን ወደ ኅሊናቸው እየተመለሱ ነው ወይስ አዲስ የማጥመጃ ሥልት ቀይሰው ወደባሰ ስቃይ ሊያወርዱን ነው በሚል በጥርጣሬ ሲታይ ነበር። የትምህርት ሚኒስትሩ የመምህራን  ጥያቄ በሚመለከተው አካል አማካይነት ምላሽ እንደሚያገኝ በተለመደው የወያኔ ባለስልጣናት የሽወዳ መልስ የሰጠ ቢመስልም ጉዳዩን አንስቶ እዚህ ደርሷል የሚል አልተገኘም። የኑሮ ውድነቱ ደግሞ ቆሞ የሚጠብቅ ሳይሆን ዕለት በእለት በሮኬት ፍጥነት ወደ ሰማይ የሚወነጨፍ በመሆኑና ሕልውና ላይ በማነጣጠሩ ተዕግሥቱም፤ፍርሃቱ ሁሉም ነገር ተሚጦ “ጅብ ከሚበላህ በልተኸው ተቀደስ” እንዲሉ ወያኔ ላይ መነሳቱ ግድ ሆነ።

በጎንደር የተቀጣጠለው የመብት ጥያቄ ባልተጠበቀ ፍጥነት አዲስ አበባ ደርሶ አቶ መለስ ቤተ መንግሥት ታዛ የቀረበና የሚያንቃጭል ደውል ሆኖ በመሰማቱ እበላ ባይ የካድሬ ሠራዊትና አጎብዳጅ የካቢኔ ባለሥልጣናት ሁሉ ከቢሮአቸው፤ከቪላቸውም እየወጡ ወደ ት/ቤቶች፤ትምህርት ቢሮዎች ........... ተሯሯጡ፤ተራወጡም። እዚህ ላይ አንድ ሳይጠቀስ የማይታለፍ ትዝብት እናንሳ። የትምህርቱ ጥራት በምን ደረጃ ላይ ነው?አቅርቦትና ግብአቱ እንዴት ይለካል?መምህራን፤ተማሪዎች፤ወላጆች፤ባለሙያዎችና ድጋፍ ሰጪዎች፤ባጠቃላይ በመማር ማስተማሩ (በትምህርቱ መስክ) ባለድርሻዎች(Stake holders) ያለው ግንኙነት ተግባራዊ እንቅስቃሴ አመርቂና ውጤታማ ሆኗል? በሚሉ ጉዳዮች ዙሪያ ለመወያየትም፤ለግምገማም እንዳሁኑ የት/ቤቶችንና ጽ/ቤቶችን ደጅ ያጎደጎደ የባለሥልጣን መንጋ አልታየም።ያ ሁሉ ሩጫና ማዘጥዘጥ በተለመደው የመከፋፈል ሥልት በመምህራን የተነሱ ጥያቄዎችን ለማፈን በመዶለት የተሰላ ለመሆኑ ከሕዝብ ቁጥጥር ውጪ በሆነው የወያኔ ሚዲያ የተስተጋባውን ፕሮፓጋንዳ ያየና የሰማ በቀላሉ የሚረዳው ጉዳይ ነው።

እጅግ አሳዛኙና ኅሊናን የሚያቆስለው ግን መምህሩን መስለው በመምህሩ ስም የሚጠሩ ከዚያም አልፈው ጉዳይህን እናስፈጽማለን፤እንወክልሃለን የሚሉ የበግ ለምድ የለበሱ ተኩላዎች በመምህራን መካከል ሆነው የሚያደርሱበት ጥቃትና የሚፈጽሙበት የክህደት ተልዕኮ ነው።”ተለጣፊም”ተባለ “ባንዳ” ወይም “ሆዳም” በነዚህ አስነዋሪ ስሞችና ተግባራት መጠራታቸውን እየለመዱ ከሚያገኙት ዳረጎት ጋር እየጣማቸው የሄዱ እንጂ እያፈሩበት፤እየተጸጸቱበት ለፈጸሙትም በደል ለይቅርታም የተዘጋጁ ሆነው አልተገኙም።አሁን እንኳን የወያኔ ፋሽሽታዊ ግፈኛነት ጽዋው ሞልቶ እየፈሰሰ እያለ ለማየት የሚያስችል ዓይነ ሕሊና አጥተዋል።

ለነገሩ የዓሣ ግማቱ ከአናቱ ነውና ያለመታደል ሆኖ ለአገር አንድነት ደማቸው የፈሰሰ፤አጥንታቸው የተከሰከሰ አባቶች፤እናቶች ከነርሱም በፊትም አያት ቅድመአያቶቻችን ታሪካቸው ሊወደስ ሲገባው በባለጊዜዎቹ ሲወቀስ/ሲረክስ ባንዳዎችና የልጅ ልጆቻቸው ደግሞ በለስ ቀንቷቸው በርዕስ ብሔርነትና ከዚያም በታች በተዋረደ ሥልጣን በመያዛቸው በስመ መንግሥት የተቀመጡበትን መንበር ተገን አድርገው አገሪቱን እንደ ግል አንጡራ ሀብት እየቸበቸቡ፤ወገኖቻችንን በሰልፍ ለባዕዳን በባርነት እያስፈነገሉ ነው።በዚህ ቁሙ ያላቸው አካል በመጥፋቱ”የባንዳም”ጊዜ አለው የተባለ በሚመስል እሳቤ በመስኩ የሚሰማራው ተበራክቷል።

መምህራን ገና ከጥዋቱ ተለጣፊዎች ብቅ ባሉበት ወቅት የኢመማ ልሳን በሆነችው ዜና መምህራን ጋዜጣ “ተለጣፊ ሱቆች” በሚል ርዕስ በቀረበች ግጥም ጅማሮውን በዘይቤ በማውገዝ እንደዚህ ያሉት ቡድኖችና ግለሰቦች ከዚህ ተግባር እንዲታቀቡና ወደ ህዝቡ እንዲቀላቀሉ መልዕክት አስተላልፋ ነበር። የተላለፈውን መልእክት ባለመቀበል ባንዳዎች፤ ተለጣፊዎች፤ሆዳሞች ግን አጉል በሽታ ተጠናውቷቸው ይህ በውርደት ከሚወርዱበት ገደል አፋፍ ላይ ደርሰዋል። ከበሽታው ለመዳን ቢፈልጉ ኖሮ በአሁኑ ወቅት መምህራን በችጋር እየተጠበሱ እያዩ የወያኔ አፈ ቀላጤ ሆነው ለቀረበው የሙብት ጥያቄ ተገቢ ምላሽ ተሰጥቷል ባላሉ ነበር።

በጎንደር ተጀምሮ አዲስ አበባ የደረሰው የመምህራን የሥራ ማቆም አድማ ወያኔ/ኢህአዴግን ያስራደ እንደነበረ ታይቷል።ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ በተለመደው ሸፍጥ የደመወዝ ማስተካከያ /እርከን 99.9% የሚሆኑትን መምህራን አርኪቷል ሲል በመርበትበት ለይስሙላ ፓርላማው ያቀረበው ሪፖርት አስቂኝና ካንድ ጠቅላይ ሚኒስትር የማይጠበቅ ቅጥፋት ነው።

የጠቅላይ ሚኒስትሩን ቅጥያጣ ማጭበርበርና ውሸት ግን ጉዳዩን የሚከታተለው ሕዝብ በሚገባ ያውቀዋል። ይህ ዕውነታም ከታየውና ከተሰማው ተጨባጭ ሁኔታ በመነሳት ጥቂት ነጥቦችን እናቀርባለን።የመምህራን አድማ ከመከሰቱ በፊት በየት/ቤቶች ይታዩ የነበሩትን መሰናዶዎች ለማፈን የኢህአዴግ አባል የሆኑትን መምህራን በመማጠን አወያይቶ ውጤት አልባ ስለመሆኑ እንዲያውም ጥያቄው እነርሱን ከሌሎች መምህራን ጋር የሚያቆራኝ እንደሆነ አጉልተው በማውጣት ተናግረው ጭራሹኑ የእንቅስቃሴው ንቁ ተሳታፊዎች ሆነው ተገኝተዋል።ይህ አዝማሚያ ያሰጋው ውያኔ ከት/ቤቶች ውጪ በየክፍለ ከተማዎቹ ጠርቶ እንደገና በውይይት ሓሳባቸውን ለማስቀየር ቢሞክርም ስብሰባውን እየረገጡ እስከመውጣት፤ ከድርጅት አባልነት እስከመልቀቅም ደርሰዋል።በዚህ ሙከራው የተደናገጠው ወያኔ ወደ ሌላ ማዳኛ ቢሆነኝ ብሎ ወዳሰበው የስብሰባና የማወናበጃ ዘዴ ተሻገረ።ይሕ ደግሞ ቶፕ ቴን(Top Ten) በሚል የሚታወቅ ከክፍላቸው ከአንደኛ እስከ አሥረኛ ደረጃ የወጡ ተማሪዎችን ለማወያየትና ድጋፍ ለማግኘት የመቅበዝበዝ ተግባር ነበር፡፡ስብሰባው ሲካሄድ እንዲያነበንቡ የተነገራቸውን ሸምድደው የገቡ ካድሬዎች መምህሩን በተማሪዎች ፊት ለማውገዝና ለመወንጀል የጀመሩት ..... መንግሥት አቅም በፈቀደ መጠን ያደረገላቸውን የደሞዝ ጭማሪ/ማስተካከያ በመቃወም በየት/ቤቱ የሥራ ማ ቆም አድማ እያደረጉ ስለሆነ እንዳትተባበሯቸው፤የትምህርት ጊዜአችሁን ሊያባክኑና የእናንተን የወደፊት እጣ ሊያሰናክሉ ነው በማለት መስበክ እንደጀመሩ ተረጋግጧል። ካድሬዎች ንግግራቸውን ሳያበቁ ተማሪዎች የተቃውሞ ሀሳባቸውን በከፍተኛ ድምጽ አሰምተው መድረክ ላይ የነበሩትን ሓሳዊ መሲሆች አፍ ካሲያዙ በኋላ በቅድሚያ ተሰብስበው አቋም የያዙ በሚመስልና በአስገራሚ ሁኔታ በአንድ ቃል እንድ አንድ ሰው ሆነው መምህራን የሥራ ማቆም አድማ ማድረጋቸውን እኛም እንደግፋለን። ከምንወዳቸውና ከምናከብራቸው መምህራን ልትነጥሉን አትሞክሩ እያሉ እንዳሳፈሯቸው ነው ሓቁ። መራብ መጠማታቸውን አብረናቸው ከምንውለው ከኛ በላይ የሚያውቅ የለም።ከት/ቤትስ ውጪ ወይ የቤተስቦቻችንን ቤት ተከራይተው አለበለዚያም በጉርብትናና በመኖሪያ ቀበሌ አብረን ስለምንኖር ኑሮአቸው አስከፊ መሆኑን እንዴት አናውቅም በሚል ሐሳባቸውን አጠናክረው የካድሬዎችን ተልዕኮ ውድቅ እንዳደረጉ የአደባባይ ሚስጢር ነው።

የመምህር ትልቁ ደመወዙ፤ደስታውም፤መከፋቱም በተማሪዎች ሲመሰክርለት ነው። መምህር የትም ቦታ ቢሄድ ባይተዋር አይሆንም። የመምህርን የሙያ ክብርና ቅን አገልግሎት እንኳንስ አንድ አዳራሽ አንድ ከተማም አያጠበውም። የተማሪዎችን ለመምህራን ጥብቅና መቆም ባገር ውስጥም በስደትም ያለን የሙያው ባለቤቶች ጃንሜዳ ተሰብስበን ማየት/መስማት የሚያስችል አጋጣሚ ቢፈጠር በደስታ ብዛት ሲቃ እንደሚተናነቀን በእርግተኝነት መናገር ይቻላል።ታዲያ እንደዚህ ላለ ትውልድ መስዋዕት ለመሆን የሚሳሱለት ህይወት እንዴት ሊኖር ይችላል?

ወያኔ/ኢህአዴግ ይይዘው ይጨብጠው ጠፍቶበት ከካድሬ መምህራን ወደተማሪዎች፤ከተማሪዎች ወደ ወላጆች በመመላለስ በስብሰባ ልቡ ጠፍቶ ከርሟል።በመጨረሻ ጊዜ ስብሰባ ያካሄደው ከወላጆች ጋር ነበር። ከወላጆች ጋር ስብሰባ የተደረገው መጋቢት 23/2004 ዓ.ም ነበር። የጥሪ ወረቀቱ የተላከው ከየት/ቤቱ በተማሪዎች አማካይነት ነበር። በመንግሥት ሚዲያ የተናፈሰውን ያህል ባይሆንም በርካታ ወላጆች በስብሰባው ተገኝተዋል። ስብሰባው ተጀምሮ ካድሬዎች እንደልማዳቸው መምህራንን መኮነን ሲጀምሩ ወላጆች ካድሬዎች እንዲቀጥሉም ሆነ እንዲጨርሱ ዕድል ሳይሰጡ የወያኔን ዋሾነት አንስተው አሁንም ልታሞኙን ትሞክራላችሁ?መምህራን የወር ደመወዛቸው ከ15 ቀናት በላይ አያቆያቸውም። መምህራን ልጆቻችን ናቸው፤ኑሮአቸውን እናውቃለን ፤የሚበሉትና የሚለብሱት በብድር ነው፤ይልቁንስ በቂ ደመወዝ ጨምሩላቸው፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ አይቃወምም  በማለት ቀንድ ቀንዳቸውን ብለው እንዳሳፈሯቸው የሚያውቅና የሚታዘብ ሕዝብ ያለው እዚያው አዲስ አበባ ከተማ ነው።

እንግዲህ አቶ መለስና ቀንዳኛ ካድሬዎቹ መምህራንን ከሥራ ለማባረር መዛት፤የተለየ የፖለቲካ አጀንዳ አላችሁ፤ አድማውን ከሽብርተኞች ተግባር ለይተን አናየውም ..... ማለት ከፋሺታዊ አፈናና እመቃ በቀር ምን ሊሆን እንደሚችል ፍርዱን ለኢትዮጲያ ሕዝብ እንተዋለን። የፍርዱ ቀን ግን ይፋጠን ዘንድ ዜጎች ሁሉ የበኩላቸውን መሥራት ይጠበቅባቸዋል።ይህ በእንዲህ እያለ በተለይ በፌዴራልና በክልል ደረጃ ካሉት ጥቂት ጥቅመኞች በቀር በታችኛው

የአስተዳደር እርከን ያሉት የኢህአዴግ አባላትና ካድሬዎች እየተገመሱ ወደ ብዙኃኑ መምህራን እየተቀላቀሉ እንደሆነ ይሰማል። ለወደፊትም ከአጋር የሙያ ባልደረቦቻቸውና ከህዝብ ጎን መቆም ትክክለኛ አማራጭ ይሆናል።

በቅርቡ የተደረገዉ የመምህራን የሥራ ማቆም አድማ በአሸናፊነት አለመዝለቅ አስደንጋጭም ፤ተስፋ አስቆራጪም አይደለም፤ሊሆንም አይችልም። በተደጋጋሚ ሲነገር እንደነበረው ሁሉ ወደፊትም የትግሉ ምህዋር የሚሆነው በአንድነት የመቆም ባህል ሲፈጠር ነው።አሁንም ይህ ችግር ያለመወገዱ ነው ለትግሉ ዳር መድረስ እንከን የሆነው። ያለመሰልቸት የምናሳስበው ሁነኛ ቁም ነገር ቢኖር መምህራን አሁንም በአንድነት የመቆም ተምሳሌት ሆነን ለድል እንድንበቃ ነው።ብዙ አንገት የሚያስደፉ፤ሞራል የሚሰብሩ ነገሮች ተጋርጠውብናል።በኢኮኖሚው መዋዠቅ የኑሮ ውድነቱ ደቁሶናል።የቤተሰብ ኃላፊነት ሸክሙ የመርግ ያህል ተጭኖናል። ማስፈራራት፤የሥራ ዋስትና ማጣት፤ዘለፋና ውርደት የማንሸከማቸው የግፍ ኮተቶች ሆነዋል።ይህን ስቃይና አበሳ ላካቴው ለማስወገድና ራሳችንን ነፃ ሰዎች ለማድረግ፤በነፃነት ለመደራጀትና በሙያችን ለመከበር ለመስዋዕትነት ከመዘጋጀትና በአንድነት ከመቆም ሌላ ምን ምርጫ ሊኖረን ይችላል? የቤተሰብ፤የህብረተሰብ፤ የአገር ደህንነትና ዕድገትስ በምን ተአምር ይመጣል?

ብዙ ጊዜ ለማሳየት እንደ ተሞከረው ወያኔ በሩቅ ጠላቶቻችን ድጋፍና ሁለገብ እርዳታ የመንግሥት ወንበር ላይ ሲመጣ ኢትዮጵያን ለማፈራረስና ሕዝቡን በዘረኝነት ለማናከስ ሌት ተቀን እየተጋ የተሰጠውን የቤት ሥራ ለማገባደድ የመጨረሻ ምዕራፍ ላይ የደረሰ ይመስላል።ባለን ማህበራዊ ስፍራና የሙያና የዜግነት ግዴታ እኛም በየበኩላችን የምንከፍለው መስዋዕትነትና የምናራምደው ብሔራዊ አጀንዳ አለን። ይኽን ለማረጋገጥ ደግሞ ከሌሎች ሲቪክ ማህበራትና የህብረተሰብ ክፍል ቅንጅት መፍጠርንም ይጠይቃል።ታዲያ ለዚህ ሁሉ እልህ አስጨራሽ ትግል መጀመሪያ መደራጀት ቀዳሚ ተግባር ነው።ሐቀኛው ኢመማ ባለመኖሩ ተጀምሮ የነበረው የሥራ ማቆም አድማ ለጊዜው ግቡን አልመታም።

በአሁኑ ጊዜ የመንግሥት ባለሥልጣናትና መደዴ ካድሬ ሁሉ የሚቀልድብን የሙያ ማህበራችንና አመራሩ በሆድ አደሮች በመገረኩ ነው። የወቅቱ አንገብጋቢ የትግል ስልት የማህበሩን ሕልውና እንደገና ለማረጋገጥ አመራሩን ከታች እስከ ላይ መምህራን በመረጧቸው ተወካዮች ለመተካት ስልታዊ በሆነ መንገድ መንቀሳቀስ ያስፈልጋል።ያለ አዝማች ዘማቻ መውጣት ለድል የሚያበቃ አካሄድ አይደለም። በዚህ አንፃር በወያኔ ስለላና አፈና ብዛት መድረክ ፈጥሮ በአግባቡ መሪዎችን መርጦ ማስቀመጥ የሚያስቸግር ስለሚሆን በህቡዕ ቆራጦችን ከየቦታው አጭቶ በማስቀመጥ ወሳኝ ውቅት ላይ አመራሩን እንዲይዙና በአገሪቱ በመላ ትግሉን አቀጣጥለው ለማያዳግም እንቅስቃሴና ማምለጥ የማይገባው ድል እንዲጨበጥ መጣር፤ መጣር ብቻም አይደለም ማረጋገጥም ወሳኝ ነው።

ባለፈው “ስንት ዘንድሮ ያልፍብናል” በሚል ርዕስ መግለጫ አውጥተን ይህ አመት እንዳያመልጠን ተረባርበን ነፃ እንድንወጣ በስደት የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አባላት አስተባባሪ ኮሚቴ አሳስቦ ነበር። አቶ መለስ ባስቀመጠው ስሌት እንኳን አምስት መቶ መምህራን ይህን ያህል ግፈኛውንና አፋኙን ሥርዓት ካርበደበዱ አምስት ሺህ ቢሆን ኖሮ ለካ ነገሩ አልቆ ኖሯል። አሁንም ደግሞ የምናሳስበው እስከመቼ እንራባለን?እስከመቼ እንሰደባለን?እስከመቼስ እንዋረዳለን? ስንት ጊዜስ በቁም እንሞታለን? ከእንግዲህ በቃ እንበል። ይህን በጣዕረ ሞቱ(Ghost) የሚገዛ ሥርዓት እናክትመው። ትግላችን በማስፈራራትና በውሸት ውንጀላ አይኮላሽም።በአንድነት እንቁም።

በመጨረሻም አገር ውስጥ ያሉ ወገኖቻችን ሠራተኛው፤ገበሬው፤ተማሪው፤ታክሲ ነጂው፤ነጋዴው -------- ትግላቸውን ከመምህራን ጋር እንዲያስተባብሩና ይህን ዘረኛ ሥርዓት ከና ሰንኮፉ እንዲነቅሉ ጥሪ እናደርጋለን።በውጪ ዲያስፖራው ከአሁን ቀደም ለተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶችና በትግሉ ሂደት ሰለባ ለሆኑ መሪዎች፤ለሰብአዊ መብት ተከራካሪዎች፤ለነፃው ሚዲያ አባላት፤በተለይም በሥርዓቱ አፋኝ የደህንነት ቡድን እየተለቀመ ወህኒ ቤት ለተወረወሩ ከትውልድ አገራቸው ለተባረሩ ......ያደረጋችሁትን የሞራል፣ የማቴሪያልና የፋይናንስ ድጋፍ የበኩላችንን አድናቆት እየገለጽን በአሁኑ ጊዜ ከሥራ ለተባረሩና ወደፊት በበቀል ውያኔ ለሚያባርራቸው ታጋይ መምህራን ከነቤተሰቦቻቸው በርሃብ እንዳያልቁ ለመታደግ በሚደረገዉ እንቅስቃሴ ድጋፋችሁን እንድታሳዩ እንማጸናለን።

*ወያኔ በድቡሽት ላይ የተሰራ ቤት ስለሆነ ከተባበርን በፍጥነት ይፈርሳል !*
*መምህራን የአንድነት መንፈስ መታደስ፤ የወያኔ ሥርዓት መገርሰስ !*
በዘረኝነት ላይ እንነሳ !
ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ !

ለበለጠ መረጃ በ eta1941@yahoo.com በመጻፍ ሊያገኙን ይችላሉ